# ከኮንዶምንየም ቤቶች ጀርባ ያለው ትክክለኛ ዓላማ ሲገለጥ

ፀሃፊ፡ ሰዊት ሰለሞን

ይህን ፅሁፍ ለመፃፍ የተነሳሳሁት በድህረ ገፃችሁ ላይ *"ከመንግስት ቤቶች ግንባታ ጀርባ ያለው ትክክለኛ ዓላማ ሲገለጥ"* በሚል ራሳቸውን ግርማ ሠይፍ ማሩ ነኝ በሚሉ ግለሰብ የቀረበውን ፅሁፍ ከተመለከትኩ በኋላ ፅሁፍ ሙሉ በሙሉ በሚያስችል ሁኔታ ሆነ ተብሎ ወይም ባለማወቅ በውሸትና በጥላቻ አስተያየቶች የተሞላና ከእውነት ፈፅሞ የራቀ በመሆኑ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል በሚል ምክንያት ነው፡፡ የአቶ ግርማ ፅሁፍ አብዛኛውን ህዝብ ከማሳዘን ውጭ ሌላ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ አለው ብዬ ባላምንም ጥቂቶች የዋሆችን በተለይ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ዜጎች ግን (ያነጣጠረውም እነሱ ላይ ስለሚመስል) መደናገር ውስጥ እንዳይገቡ እውነታውን ማሳየት የዜግነት ግዴታ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ይህን ማድረግ ደግሞ ኢ.ሕአዴግን የመደገፍ ወይም ያለመደገፍ ጉዳይ ሳይሆን እንደ አንድ ዜጋ የሚታይ ዕውነትን የመናገር ወይም የመካድ ጉዳይ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ የዚህ ፅሁፍ ዓላማም በቅን መንፈስ ማየት ለፈለገ ዜጋ ዕውነታውን ማሳየት ብቻ ነው፡፡

የተቀናጀ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ወይም በተለምዶ ኮንዶምንየም የምንላቸው ቤቶች ግንባታ ሲታለም በዛ ያሉ ዓላማዎች ያለው ሲሆን ዋናው ዓላማ ግን **በከተሞች ውስጥ ያለውን የቤት ዕጥረት መቅረፍ ነው፡፡** ይህ መሆኑን የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በየአጋጣሚው የገለፁት ሲሆን ከዚህ ዋና አላማው በተጨማሪ ሌሎች ትርጉም ያላቸው ጥቅሞችንም እንዲሰጥ የታለመ መሆኑ በግልፅ ይታወቃል፡፡ እነዚህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

- ከፍተኛ የሆነ የሥራ ዕድል መፍጠር አንዱ የፕሮግራሙ ዓላማ ሲሆን በዚህ ፕሮግራም ከ100,000 በላይ የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል፡፡
- የህዝቡን የቁጠባ ባህል ማሳደግ ሌላው የፕሮግራሙ ዓላማ ሲሆን በዚህ ረገድ የከተማው ነዋሪ የመቆጠብ ባህል እንዲያድግ አግዟል፡፡

- የኮንስትራክሽን ሴክተሩን ማሳደግ ሌላ አላማ ተደርጐ የተወሰደ ሲሆን በዚህ ረገድ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በግላቸው ወይም በመደራጀት የሚሰሩ ኮንትራክተሮች፣ ኮንሰልታንቶች እና የኮንስትራክሽን ዕቃ አቅራቢዎች ተፈጥረዋል፡፡
- ያረጁ የከተማ ክፍሎችን ማደስ ሌላው ትልቅ ዓላማ ሲሆን የልደታን መልሶ ግንባታ ውጤት መመልከት ብቻ ለዚህ በቂ ምስክር ነው፡፡
- ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ደግሞ ሌላው ዓላማ ሲሆን ከግዜ ወደ ግዜ አማራጮችን በማስፋት ቤት አልባውን ነዋሪ ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል፡፡

ከዚህ ውጭ ፕሮግራሙ ሌሎች በዛ ያሉ ጥቅሞች እያስገኘ መሆኑን በቅን ልቦና ለተመለከተው መረዳት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ የተሻለ የመሬት አጠቃቀም መፍጠር፣ ወደ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ መሸጋገር፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት የተሻለ መሆን፣ የተሻለ የከተማ ዕይታ መፈጠሩ አሌ ሊባሉ የማይችሉ ዕውነታዎች ከፕሮግራሙ የተገኙ ጥቅሞች ናቸው፡፡

ዕውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ፀሃፊው "ሰሞኑን ህዝብን እያመሰ ያለ ጉዳይ" በማለት ሊያጥላሉት የሞከሩ ሲሆን ከጅምሩ ***የመንግስት የቤቶች ግንባታ*** በማለት ፕሮግራሙን መጥራታቸው ከመሠረቱ ስህተት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ የሚገነቡት ቤቶች መንግስት ባለበት የዜጎችን መኖሪያ ቤት ችግር የመቅረፍ ኃላፊነት ካቀዳቸው የተለያዩ ዕቅዶች መሃል አንዱ ሆኖ ተግባራዊ እየተደረገ ያለና ኮንደሚኒየም ቤቶቹ ተገንብተው ለባለዕድሎች እየተላለÕ የሚገኙ መሆኑ ፀሃይ የሞቀው ሃቅ ሆኖ እያለ ቤቶቹ በመንግስት ቁጥጥር ሥር እንዳሉ ተደርጐ መቅረቡ ቅጥፈት ነው፡፡ በቅርቡ ምዝገባ የተደረገባቸው 10/90፣ 20/80 እና 40/60 ቤቶች ፕሮግራም ለከተማው ነዋሪ ከቀድሞው የበለጠ ከፍተኛ ተስፋና አማራጭ የፈጠሩ መሆናቸውንና ከህዝቡ ፍላጎት አኳያ ለመንግስትም ዕውቀት የሰጡ መሆናቸውን መመልከት ተቻለ እንጂ መተራመስ የሚባል ነገር አልታየም፡፡ አቶ ግርማ መተራመስ ያሉት ሰልÕን ይሆን? ይህ ሰልፍ ደግሞ የህዝቡ ፍለጐት እንጂ መደናገርን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የትችቱ አቅራቢ በእርግጥ ኢትዮጵያዊ ስለመሆናቸው እስከመጠራጠር የሚያደርሰው ካልሆነም ለዚህች ሃገር በጎ አሳቢ እንዳልሆኑ በግልፅ የሚያሳየው ***የኢህአዴግ መንግስት በምንም ዓይነት መለኪያ ለኢትዮጵያ ህዝብ የመኖሪያ ቤት ሰርቶ የመስጠት አቅምም ሆነ ፍላጐት የለውም*** በማለት አቋማቸውን የገለፁበት አባባል ነው፡፡

መንግስት ያለውን አነስተኛ የፋይናንስ አቅም አሟጦ ይህን የቤት ፕሮግራም በመጀመር መቶ ሺዎችን ተጠቃሚ ማድረጉና በጣም ቅርብ ሊባል በሚችል ግዜ ደግሞ ሌሎች መቶ ሺዎችን ተጠቃሚ ማድረግ በሚያስችለው ቁመና ላይ መገኘቱ በእርግጥ መንግስት ለህዝቡ የመኖሪያ ቤት የመሥራት ፍላጎት እና አነስተኛም ቢሆን አቅም ስለሌለው ነው? አቶ ግርማ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩትን ኢትዮጵያዊያን የቤት ዕድል ተጠቃሚዎች ምን ይሏቸዋል? ለምንስ ይህን ማየት አልፈለጉም? ልብ ይበሉ፤ በዚህ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም የኢህአዴግ መንግስት የከተማ ነዋሪዎችን የቤት ዕጥረት ለማቃለል እያደረገ ያለው ጥረት እርስዎ እንዳሉት ሳይሆን በዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር የተመሰገነበትና የተደነቀበት ብሎም እንደ ጥሩ ልምድ (best practice) ተወስዶ በውጭ ሃገር ባለሥልጣኖችና ባሙያዎች እየተጎበኘ መሆኑን ቢነገርዎት መርዶ ይሆንብዎት ይሆን? ለዚህም እንደማሳያ አንዱን ብቻ እንኳን ለመጥቀስ ያህል “ Condominium Housing in Ethiopia” በሚል የተባበሩት መንግሥታት አንድ አካል የሆነው UN-HABITAT ያሳተመውን የጥናት ሰነድ ድረገፆች ውስጥ በቀላሉ ሊያገኙት ይችላሉና በእርግጥ ሀቁን መረዳት ከፈለጉ እንዲያነቡት እመክራለሁ፡፡ ከዚህ ውጭ በኮንዶምንየም ቤቶች ፕሮግራም ላይ ለቁጥር በዛ ያሉ ጥናቶች አውሮፓ ውስጥ በሚገኙ ታዋቂ ዩንቨርስቲዎች እንደመመረቂያ ፅሁፍ የተሠራባቸው መሆኑን ያውቁ ይሆን? ይህንንም በተለያዩ ድረገፆች ፍተሻ ቢያደርጉ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

ሌላው አቶ ግርማ ያነሱት ሀሳብ ***“የኢህአዴግ መንግስት በአለም ላይ ካሉት መንግስታት በተለየ ሁኔታ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቤቶችን እንደ ኮንትራክተር ለመገንባት ሙከራ እያደረገ ያለ መንግስት ነው”*** በማለት ቀደም ብለው መንግስት የቤት ፍላጎት የማሟላት ፍላጎት የለውም ያሉትን በተቃረነ መልኩ መንግስት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቤቶችን ልስራ እያለ ነው ብለዋል፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት መንግስት ኮንትራክተር ሆኖ እየሰራ ሳይሆን በነባርና በሂደቱ በተፈጠሩ አዳዲስ ኮንትራክተሮች ቤቶችን እያሰራ መሆኑ እና የኢትዮጵያ መንግስት ብቻ ሳየሆን በሌላው ዓለምም የህዝባቸውን የቤት ዕጥረት ምላሽ ለመስጠት የፈለጉ ሃገሮች እንደ ነባራዊ ሁኔታቸው እየተገበሩት ያለ ጉዳይ ነው፡፡

ፀሃፊው በማስከተል ***መንግስት  የቤት አቅርቦት ላይ ምን አገባው፣ ያለስራው ገብቷል*** በማለት መንግስትን ሊኮንኑ ሞክረዋል፡፡ ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች መሃል አንዱ መጠለያ መሆኑ ይታወቃል፡፡ መንግስት ይህን የነዋሪዎች መሰረታዊ ችግር ለመፍታት ፖሊሲ ከመቅረፅ ጀምሮ አቅሙ በፈቀደ መጠን ቤቶችን ሰርቶ የማቅረብ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር አለበት፡፡  ይህንን ግዴታውን በመገንዘብ ይመስለኛል መንግስት ከፍተኛ ድጎማ በማድረግ የኮንደሚንየም ቤቶችን እየሰራ ያለው፡፡ ፀሃፊው እንዳሉት መንግስት መሬት እየቸበቸበ ሳይሆን የኮንደሚንየም ቤቶች ለተገነቡባቸው የከተማ ቦታ ክፍያ የማያስከፍል መሆኑን ያውቁ ይሆን?

ሌላው ፀሃፊው ያነሱትና ፈፅሞ ከሃቁ የራቀው መንግስት ለነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚውል ፋይናንስ በባንክ ብድር መልክ እንዲሰጥ አላመቻቸም የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ መንግስት የኮንደሚንየም ተጠቃሚዎች ከቅድመ ክፍያ ውጭ ከቤቱ ዋጋ አብዛኛውን መጠን ከባንክ በብድር ወስደው በወርሃዊ ክፍያ መልክ በረዥም ጊዜ እንዲመልሱ የፈጠረውን ዕድል ምን ይሉታል?

አቶ ግርማ የቤቶች ፕሮግራም ዋና አላማ ***መንግስት የውጭ ምንዛሬ እንዲያገኝ በማድረግ የራሱ ዕቅድ (የቤቶች ልማትና ሌሎችን የመንግስት ትልልቅ ዕቅዶች ማለታቸው ነው) ተግባራዊ በማድረግ የግሉን ሴክተር ከጨዋታ ውጭ ለማድረግ ነው*** በማለት ያለ እፍረት ፅፈዋል፡፡ በቀና ልቦና ከታየ መንግስት ደጋግሞ እንደሚገልፀው የግሉ ሴክተር ባልገባበት ወይም በሚፈለገው መጠን ባልተሳተፈበት የልማት መስክ ላይ የጎደለውን ቢሞላ ክፋቱ ምን ላይ ይሆን? ለዚህም ማስፈፀሚያ የሚሆን የተለያዩ የፋይናንስ ምንጮችን ቢያመቻች ሃጢያቱ ምንድን ይሆን? መንግስት እያደረገ ያለው በተቃራኒው ለግሉ ሴክተር ማደግ ብር ከፋች የሚሆኑ ስራዎችን መስራት ይመስለኛል፡፡ ነገሩ ለሃገሪቱ ክፋት ከመመኘት የተሰጠ መርዛማ ሃሳብ በመሆኑ ምክንያት ምንም ቢሰራ ከማጥላላት ያለፈ ቀና አስተሳሰብ ከኚህ ፀሃፊ ከመጀመሪያውኑ አይጠበቅም፡፡

የአቶ ግርማ ሌላኛው አስቂኝ አስተያየት ደግሞ መንግስት ኮንደሚንየም ቤቶችን የሚሰራው ዜጎችን በአንድ አካባቢ አጉሮ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ነው ብለዋል፡፡ ለዚህ እንደማሳያ ያቀረቡት ቤቶቹን መሸጥ አይቻልም በማለት የሰጡት ምክንያት ነው፡፡

ይህ ፍፁም የኢትዮጵያን ሁኔታ ከሚረዳ ጤነኛ አዕምሮ የወጣ ሃሳብ አይደለም፡፡ ከጀምሩ መንግስት ቤት የሚሠራው ዜጎችን አጉሮ ለመቆጣጠር ነው የሚል ሃሳብ ጤነኛ አለመሆኑና ፍፁም ቅጥፈት መሆኑን መረዳት ምርምር የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ አሁን በሥልጣን ላይ ካለው የኢትዮጵያ መንግስት ባህርይ የሚታሰብ አይደለምና፡ ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ዕድሉ አጋጥሞአቸው ቤቱ ከተላለፈላቸው ነዋሪዎች መሀል ቀላል ቁጥር የማይባሉት ማንም ጠያቂ ሳይኖርባቸው ቤቱን መሸጥ በሚያስብል ሁኔታ በዋስትና ያስያዙ መሆናቸውና ሌሎችም ብዙዎች አከራይተው በፈለጉት ሌላ አካባቢ የሚኖሩ መሆናቸው ነው፡፡ ባለዕድሎች የመሸጥ መብታቸው ለአምስት ዓመታት ብቻ የተገደበ መሆኑንስ ለምን ዘለሉት? ይህም የተደረገው ሌላ ሚስጥር ኖሮት ሳይሆን ሁሌም ቀዳዳ ፈላጊውን ኪራይ ሰብሳቢ ደላላ እና ሳይሰራ መበልፀግ የሚፈልገውን ነጋዴ ለማገድ ሲባል መሆኑ ተደጋግሞ የተገለፀ ጉዳይ ነው፡፡ አቶ ግርማ አምስት ዓመት የሞላቸው ቤቶች እኮ በሽያጭ እየተላለÕ መሆኑን አልሰሙ ይሆን?

አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት እንዲሉ የፀሃፊው ዋና አላማ መንግስትን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ጥላቻ በመሆኑና ይህንንም ተፈፃሚ ያደረጉ መስሎአቸው ያቀረቡት መሆኑ በፅሁፋቸው በመጨረሻ ላይ በቁጭት መልክ ***ለነፃነት እንጂ ለምን ለኮንዶምንየም እንሰለፋለን*** የሚል ቃና ያለው ሃሰብ ማቅረባቸው ሁኔታቸውን ወዴት ወዴት ያስብልባቸዋል፡፡

የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ለከተሞች የቤት ዕጥረት መፍትሄ ከመስጠት አኳያ የጎላ ድርሻ እየተጫወተ ያለ በመሆኑና በተለይም የዝቅተኛ ገቢ ነዋሪውን የቤት ችግር ለማሟላት በወሳኝ መልኩ የሚያግዝ በመሆኑ መንግስት በያዘው ዕቅድ መግፋት አለበት፡፡ ይህ ፕሮግራም የቤት ችግርን በዋነኛነት ከመመለሱ በተጨማሪ ያረጁ የከተማ አካባቢዎችን በመቀየር የከተማ ነዋሪውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ትርጉም ባለው ሁኔታ እያሻሻለ ሲሆን ዜጎችም የተረጋጋና ተስፋ ያለው ህይወት እንዲኖሩ እያደረገ ይገኛል፡፡

በመጨረሻም ላነሳ የምፈልገው ጉዳይ፣ የማንኛውም ወገን አስተያየትና አቋም ለህዝብ መቅረቡ ተገቢ ሆኖ እያለ የሚቀርበው ፅሁÕ ግን በእውቀት እና እውነት ላይ የተመሠረተ ትንተናና ጥልቀት ያለው መሆን ለሰለጠነ የሃሳቦች ክርክር መሠረት ሊሆን ስለሚችል ሚዛን የሚደፉ የተቃውሞም ይሁን የድጋፍ ሃሳቦች እየተመረጡ ቢቀርቡ ይሻላላ ባይ ነኝ፡፡ የአቶ ግርማን "በሬ ወለደ" አይነት ፅሁፍ ግን ምንም እርባና የሌለው በመሆኑ በድረገፃችሁ ቦታ ሊሰጠው ባልተገባ ነበር ባይ ነኝ፡፡

<u>ማስታወሻ፡</u>

የዚህ አስተያየት አቅራቢ የከተማ ፕላንና የከተማ ማኔጅመንት ባለሙያና በአንድ አውሮፓዊ ዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት ውስጥ በፕሮጀክት አስተባባሪነትና በሲኒየር አማካሪነት ሰራተኛ ስትሆን ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጋር ንኪኪ የሌላትና ለህሊናዋ ብቻ ተገዥ የሆነች ኢትዮጵያዊት ነች፡፡